11 ኛ ዓመት ቁጥር 21
11 th Year No. 21

ባህርዳር ሐምሌ 20 ቀን 1998 ዓ.ም
Bahir Dar 27 July,2006

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ
# ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር **160/2001** ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የማራ ክልል ሕዝቦች ሰማዕታት መታሰቢያ ሐውልት ጽህፈት ቤትን ለማቋቋምና አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

**Issued under the auspices of the Council of the Amhara**

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 1.3 0

## አዋጅ ቁጥር **160/2001** ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልልላዊ መንግስት የማራ ክልል ሕዝቦች ሰማዕታት መታሰቢያ ሐውልት ጽህፈት ቤትን ለማቋቋምና አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የሰማዕታት ሀውልት የማራ ክልል ህዝቦች የህዝባዊ ተጋድሎና መራራ ትግል ፅናት መግለጫ ህያው ምስክር ሆኖ፣ የአማራ ህዝቦች እንደሌሎች ዒትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ለሰላምና ዲሞክራሲያዊ

ሥርዓት ምስርታ ከትጥቅ ትግል ጀንሮ ያደረጉት ፀረ-ፋሽስታዊ ደርግ መራራ ተጋድሎ በታሪካቸው ውስጥ ወሳኝ ምዕራፍ የያዘ በመሆኑ፣

በትግል ሂደት መስዋት የሆ ቁርጠኛ የህዝብ ልጆች ለደረስንበት ሰላምና ዲሞክራሲ መሠረት መሆናቸውን ማስታወስ ዘላቂ ሰላም ለማስፈንና ዴሞክራሲዊ ሥርዓትን ለመገንባት ያለው ፋይዳ የላቀ መሆኑ በመታመኑ፣

የማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንጽ 3/1/ ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጡቷል

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአማራ ክልል ሕዝቦች ሰማዕታት መታሰቢያ ሐውልት ጽፈህት ቤት ማቋቋሚያና አደስተዳደሩን መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 160/2001 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።



የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1."ሰማዕታት ሀውልት" ማለት ብአዴን ከአባላቱ ፣ ከሰራዊቱ፣ እንዲሁም ከደጋፊ ባለሀብቱ ገንዘብ በማሰባሰብ በባህርዳር ከተማ ቀበሌ 11 ክልል የማራ ክልል ህዝቦች ሰማዕታትን ለመዘከር ያሰራው ሀውልት።

2. "ብአዴን" ማለት ብሔር አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ማለት ነው።

2 "ምክር ቤት" ማለት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት መሠረት የተቋቋመው የክልሉ ምርክ ቤት ነው።

3 "መንግስት " ማለት የማራ ብሔራዊ ከክልላዊ መንግስት ማለት ነው።

4 " አማካሪ ቦርድ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 መሠረት

የተቋቋመው አማካሪ ቦርድ ማለት ነው።

5 “ማኔጅመንት ፕላን ማለት የሀውልቱን ጥበቃ፣ ላማት አገልግሎት የሚሰጥበትን ሁኔታናአስተዳደር የሚያሳይ የእቅድሰነድ ነው።

6 “ ቢሮ” ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስትየባህልና ቱሪዝም ቢሮ ነው።

ክፍል ሁለት

ስለ አማራ ክልል ህዝቦች ሰማዕታት መታሰቢያ ሀውልት ጽህፈት ቤት መቋቋም፣ ተጠሪነት፣

ዓላማ፣ ሥልጣንና ድርጅታዊ አቋም

3. መቋቋምና ተጠሪነቱ

**1.** ስለ አማራ ክልል ህዝቦች ሰማዕታት መታሰቢያ ሀውልት ጽህፈት ቤት /ከዚህ በኋላ ጽህፈት ቤቱ እየተባለ የሚጠራው /ራሱን የቻለ ህጋዊ ሰውነት ያለው የክል መንግስት ተቋም ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት ተቋቁሟል።

**2.** የጽፈት ቤቱን ተጠሪነቱ ለቢሮው ይሆናል።

**4.** ዓላማ

የሐውልቱን ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ውበት በመጠበቅ የሰላም” የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ተምሳሌት በመሆን ድህነትን ለማስወገድ በሚደረገው ጥረት ተገቢ ሚና በመጫወት የብአዴን አሻራ የሚያፀባርቅበት አግባብ አማራ ክልል ህዝቦችን ተቃሚነት ማረጋገጥ ነው።

## 5. መደበኛ አድራሻ

የሐውልቱ ጽህፈት ቤት በደመኛ አድራሻ ባህር ዳር ከተማ ይሆናል።

## 6. ስለ ጽህፈት ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት፣

ጽህፈት ቤቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉትን ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. የሰማዕታት ሀውልትንና በስሩ የሚገኙ ሌሎች ንብረቶችን ያስተዳድራል፣ይንከባከባል፣የተሻለ አገልግሎ ለተጠቃሚው የሚቀርብበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣
2. በሐውልቱ ጥበቃ ልማትና አጠቃቀም ረገድ እቅዶችን ያቅዳል፣ ይመራል፣ ያስፈጽማል፣
3. የሐውልቱን ማኔጅመንት ፕላን ያዘጋጃል፣አፈፃፀሙንይከታተላል ይመራልይ ቆጣጠራል፣
4. ኣላማውን መሠረት ያደረገ የጥናትና ምርምር ስራ ያካሂዳል፣ እንዲካሄድ ያደርጋል፣
5. ገቢውን ላመሳደግ የሚያስችሉ ተግባራትን ያስፋፋል፣
6. በህዝቡ ታሪክ ባህልና በአዴን ህዝባዊ ትግል የላቀ ጥናትና ምርምር ላደረጉ ሰዎች ሽልማት የሚያገኙበትንና የሚበረታቱበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
7. የክልሉን ያለፈ ትግል ሂደት ሚያሳይ የመረጃ ሀብት በማሰባሰብ፣ በማደራጀታና በመንከባከብ ጠብቆ ለማገናዘቢያ እንዲያውል ያደርጋል፤
8. ህውልቱን የቱሪዝም መስህብ እዲሆን ሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ለጐብኝዎች እንዲያውቁት እና እንዲጐበኙም የደርጋል፣
9. ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለሚሰጠው አገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል፣
10. የክልሉ መንግስት ሀውልቱ ሲረከብ የባውን ግዴታ ስምምነቱን መሠረትተግባራዊ ያደርጋል፣
11. በሕግ መሠረት ውሎችን ይዋዋላል፣ ስምምነቶችን ያደርጋል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣ የንብረት ባለቤትነት ይሆናል፣
12. ሀውልቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት የሚያግዙ ሌሎች ተዛማጅ

ተግባራትን ያከናውናል።

7. ስለ ጽህፈት ቤቱ ድርጅታዊ አቋም

ጽህፈት ቤቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት አካላት የረኖሩታል፡-

1. ያማካሪ ቦርድ
2. በርዕሰ መስተዳደሩ የሚሾሙ ሥራ አስኪያጆችና



3. ለስራው የሚያስፈለረጉ ሌሎች ሰራተኞች።

8. ስለሥራ አስኪያጁ አሰያየም፣ተግባር እና ኃላነፊት

ሥራ አስኪያጁ በቢሮው አቅራቢነት በርዕሰ መስተዳደሩ የሚሾም ሲሆን የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. ጽህፈት ቤቱ ዋና አስፈፃሚ ሆኖ ቢሮው በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት የሀውልቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 መሰረት ለጽህፈት ቤቱ የተሰጡትን ተግባራትና ኃላፊነቶች ሥራ ላይ ያውላል።
3. አግባብነት ያለውን ሕግ መሠረት በማድረግ ለስራ የሚያስፈልጉትን ሌሎች ሰራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል።
4. ለጽህፈት ቤቱ በጀትና የሥራ ዕቅድ በማዘጋጀት ለክልሉ

መንግስታ ያቀርባል፣ ሲፈቀድና ሲፈቀድናሥራ ላይ ያውላል።

5. ለጽህፈት ቤቱ ከተፈቀደለት በጀት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፣ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ጽህፈት ቤቱን ይወክላል።
6. የጽህፈት ቤቱን የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቢሮው ያቀርባል።

**7.** ሌሎች በቢሮ የሚሰጠውን ተግባራት ያከናውናሉ

8. ሰለ አማካሪ ቦርድ አሰያየምና ስልጣን

1. ጽህፈት ቤቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠውን ተግባር ኃፊነቶችን ለመወጣት እንዲያስችለው የሚያማክረው /ከዚህ በኋላ ቦርድ እየተባለ የሚጠራ/ አማካሪ ቦርድ በዚህ አዋጅ ተቋቋሟል።

የቦርዱ ተጠሪነቱ ለክልሉ ርዕሰ መስተዳደር ይሆናል።

2.ቦርዱ አግባብነት ካላቸው መስሪ ቤቶች በቢሮው አቅራቢነት በርዕሰ መስተዳደሩ የሚሰየሙና ቁጥራቸው ከ 5-7 የሚሆኑ አባላት ይኖሩታል። የአባላቱ ስብጥርም፡-

ሀ.የክልሉ መንግስት

ለ. የብዙሃን ማህበራት ተጠሪዎች

ሐ. የሰማእታት ቤተሰቦች

መ. ጥረት

ሰ. የባህር ዳር ከተማ አስተዳደር

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ እንድንጠብቅ ሆኖ ርዕሰ መስተዳደሩ አስፈላጊ ሆነ ሲያገኘው ከጽህፈት ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት ጋር ግንኙነት አላቸው ብሎ ያመነባቸውን አካላት የቦርድ አባል ሊያደርግ ይችላል።

በ 4. የቦርዱ ሰብሳቢ የሚሰየሙ በክልሉ ርዕሰ መስተዳደር ሆኖ የጽህፈት ቤቱ ሥራ አስኪያጅ የቦርዱ ፀሐፊ ይሆናል።

5. ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

ሀ/ በህውልት ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም እንዲሁም በአግባቡ ለክልሉ ህዝብ ጥቅም ስለሚሰጥበት መክር ይሰጣል፣

ለ/ የሀውልት ማኔጅመንት ፕላል ዝግጅትና አፈፃፀም ሁኔታ አስመልክቶ ያልተቀጠበ ምክሩን ይለግሳል፤

ሐ/ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በቅንጅትና በስልጠና የሚጠበቅባቸው ሀኃፊነት በአግባቡ ሊወጡ የሚችሉበትን አሰራር ስልት ያማክራል።

10. ስለ ቦርዱ የስብሰባ ጊዜና የውሳኔ አስጣጥ ሥነሥርዓት

1. ቦርዱ በስድደስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል። ሆኖም እንደ አስፈላጊነት አስቸኳይ ስብሰባዎችን ከማድረግ ይህ ድንጋጌ አያግደውም፤

2. ከቦርዱ አባላት መካመል ከግማሽ በላይ የሚሆት በስብሰባው

ላይ ከተገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይሆናል፤

3. በስብሰባው ከተገኙት መካከል ከግማሽ ባላይ የሆኑት አባላት የደገፉት የቦርድ ውሣኔ ይሆናል፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1-3 የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሁነው ቦርዱ የራሱን ዝርዝር የስብሰባና የአሰራር ሥነ-ሥርዓት መወሰኛ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

11. ስለ ሀውልት ማኔጅመንት ፕላል ዝግጅትና

አፈፃፀም

1. ሀውልት ማኔጅመንት ፕላል በጽህፈት ቤቱ አማካኝነት ተዘጋጅቶ ለቢሮው ቀርቦ ከፀደቀ በኋላ በሥራ ላይ የረውላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚዘጋገጀው የማኔጅመንት ፕላን ለሀውልቱ ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም በሚያመች አኳኋን ሆኖ፣ ሀውልቱን የመጠበቅ፣ የማልማትና ተፈላጊ አገልግሎት የመስት ሥራዎች በምን አይነት መርሆዎችና አስራሮች መከናውን እንደሚገባቸው ለይቶ የሚያሳይ ይሆል።
3. የተዘጋጀው የማኔጅመንት ፕላን ረቂቅ ከመፅደቁ በፊት ለሚመለከታቸው አካላትና ለአካባቢው ህዝብ ይሆናል።

**13** ስለ ሂሣብ መዛግብትን አያያዝ

1. ጽህፈት ቤቱ የተሟሉና ተክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል፣
2. የጽህፈት ቤቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶችን በክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ወይም ቦርዱ በሚሰይማቸው የውጭ ኦዲተሮች በየአመቱ ይመረምራሉ።

**13.** መብትና ግዴታን ስማስተላለፍ

**1.** በዚህ አዋጅ መሠረት የጽህፈት ቤቱ ከመቋቋሙ በፊት

ከአማራ ሰማዕታት መታሰቢያ ሐውልት ጋር በተያዙ የሚገኙ መብቶችና የተጣሉ ግዴታዎች የመታሰቢያ ስምምነቱ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ወደ ክልሉ መንግስት ተላልፈዋል፡፡

2. ሐውልቱ ከሰማዕታት አደራ ማስተላለፊያነቱ በተጨማሪ ለክልሉ ህዝብ አገልግሎት እንዲሰጥ የተሠራ በመሆኑ የባለቤትነት መብቱ የተላለፈለት የክልሉ መንግስት በማንኛውም መልኩ ዓላማውን የመቀየር ወይም ከዓላማው ውጭ ሌላ ተግባር ማከናወን አይችልም፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ስር የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አስረካቢ አካል ከአማላው ውጭ የሆነ ተግባር ተከናውኗል ብሎ ባመነ ጊዜ ሀውልቱ እንዲመለስለት የመጠየቅ መብት ይኖረዋል፣ ሀውልቱንና በውስጡ የሚገኙትን ልዩ ልዩ ንብረቶችንና ተቋማት መልሶ ይረከባል፤ ለደረሰው ጉዳትም ካሣ በሕግ መሠረት ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

**14.** ስለ ልዩ መብት

1. ሀውልቱን ለማሰራት ድጋፍ ላደረጉ፣

በግንባታው ለተባበሩ እንዲሁም

ለሰማዕታትና ለታጋይ ቤተሰቦች

በመንብኘትም ሆነ ድጋፍ በማግኘት ረገድ

ልዩ መብት ይኖራቸዋል፤

1. ልዩ መብት ያላቸው ግለሰቦች፣ የታጋይ እና የሰማዕታት ቤተሰቦች የክብር ካርድ የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡

16. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

1. የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ ሙሉ ተፈፃሚነት የሚያስፈልገውን ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

2. ቢሮው አዋጁን ተከትሎ የሚያወጣውን ደንብ ለማስፈጸም

የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

**17.** ተፈፃሚነት ስለ ሚኖራቸው ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ ደንብ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

18 አዋጁ ስለ ሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

ባህርዳር

ጥር **26** ቀን **2001** ዓ.ም

አያሌው ጐበዜ

የአማራ ብሔራዊ ክልል

ፕሬዚዳንት